# የ ማ ተ ብ ማ ሠ ር ል ማ ድ

## መ ግ ቢ ያ

ማተብ (ማዕተብ) አንደኛው ፍች ምልክት ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ቡራኬ ማለት ነው ፤ ሥርወ ግሡም « አተበ » አመለከተ ፤ ባረከ የሚለው የግዕዝ ቃል ነው ። ምልክት ሁል ጊዜ አንዱን ነገር ከሌላው ለመለየት የሚያስችለው በመሆኑ ዓለም ይጠቀምበታል ። ሐዋርያው ጳውሎስ ወደ ሮሜ ሰዎች በጻፈው መልእክቱ በአራተኛው ምዕራፍ ስለ አብርሃም ሲናገር «ሳይገረዝም በነበረው እምነት ያገኘው የጽድቅ ማኅተም የሆነ የመገረዝን ምልክት ተቀበለ» ብሏል ። ወላጆችም መንታ ሲወልዱ የትኛው ቀድሞ እንደተገኘ ለማስታወስ ምልክት ያደርጋሉ ። ለምሳሌ በአራቱ ፋሬስና ዛራ ሲወለዱ አዋላጅዋ ቀድሞ በተወለደው አውራ ጣት ላይ ክር አሥራበት እንደነበረ ይነገራል ።

## የትመጣው በታሪክ መልክ

የኢትዮጵያውያን ክርስቲያኖች ማተብ ማሠር ልማድ የመጣው ለረዥም ጊዜ የቤተ ክርስቲያናችን ሞግዚት ሆና ከቆየችው ከእስክንድርያ ቤተ ክርስ ስቲያን ነው ። በእስክንድርያው ሊቀ ጳጳስ ቴዎዶስዮስ ዘመን በሀገሩ የነበረው ዐላዊ ንጉሥ በመሆኑ የክርስትናን አስተማሪዎች እያሠረ ያስደበድብ ነበር ። ስለዚህም ቴዎዶስዮስ ካልሆነ ሰው ጋር ተጋፍጦ ከመቀሰፍና ሥራን ከማቋረጥ ዘወር ብሎ መዓቱን ማሳለፍ ይሻላል በማለት ሲሸሽ ፤ ያዕቆብ ዘእልበረዳኢ የሚባል ለክርስትና ትምህርት ቀናተኛ የሆነ ሐዋርያ በሽሽግ ያስተምር ነበር ። ይህንም የተቀደሰ ሥራውን ለማሰናከልና ለማቋረጥ የሚሹ አንዳንድ ቦዘን ተኞች በስብሰባው ላይ እየተገኙ ያስተማራቸውን ያስቱበት ያሻክሩበት ስለነበር የርሱ የሆኑትን ለይቶ ለማወቅ ሲል በአንገታቸው ላይ አድርገው ለምልክት ነት እንዲጠቀሙበት ማተብ አሠረላቸው ፤ ያሠረላቸውም ማተብ ሦስት ዓይ ነት ባንድ ላይ የተገመደ ሲሆን ጥቁር ፤ ቀይ ፤ ብጫ ነበር ። ይኸውም ጥቁሩ መከራ ፅቀበላለሁ ፤ ቀዩ ደሜን አፈሳለሁ ፤ ብጫው ትንሣኤ ሙታንን ተስፋ አደርጋለሁ የሚል እንደነበረ ይነገራል ። ያዕቆብ ዘእልበረዳኢም ያስተምር የነበረበት ዘመን አምስተኛው መቶ ዓመት እንደነበረ ይገመታል (ሃይማኖተ አበው ፤ ድርሳነ ያዕቆብ ።)

## በቤተ ክርስቲያን በኩል ያለው መልክ

ከሣቴ ብርሃን ሰላማ በአራተኛው መቶ ዓመት ወደ ሀገራችን መጥቶ የክርስትና ትምህርት ፋናን ሲተክል ያመነ የተጠመቀውን ካላመነው ለመለየት ከግንባሩ ላይ በመብጣት መስቀልኛ ምልክት ያደርግ ነበር ይባላል ። ግን የመብጣቱና ደም የማፍሰሱ ዘዴ በሕዝቡ ዘንድ ሙሉ በሙሉ ስለአልተደገፈ ከጊዜ በኋላ እንደቀረ ይነገራል ። አሁንም ሳይቀር ሸሚናውያን ከግንባራቸው ላይ ምልክት የሚታይባቸው ከዚሁ ሲያያዝ መጥቶ ነው ይባላል ።

ምንም እንኳን መቼ እንደተጀመረ ከስንተኛውም መቶ ዓመት ጀምሮ እንደምትሠራበት በቂ መረጃ ባይገኝም ቤተ ክርስቲያናችን የማተብ ማሠርን ልማድ በደንብ ታከብራለች ፤ በቤተ ክርስቲያናችን ሥነ ሥርዓት መሠረት አንድ ሕፃን ወይም አንድ ሰው ሲጠመቅ ሦስት የተለያየ ቀለም ያላቸው ፈትሎች ከአንድ ላይ ተገምደው ለዚሁ የተወሰነው ጸሎት ተደርሶባቸው ለተጠማቂው ይታሠሩለታል ፤ ክሩም ነጭ ቀይና ሰማያዊ ሲሆን ፤ ነጩ ሐዲስ ሕግን/ ወንጌልን/ እጠብቃለሁ ፤ ቀዩ በክርስቶስ ፍጹም ድኅነት እንደማገኝ አምናለሁ ፤ ሰማያዊውም ሰማያዊ ሕግን በመጠበቅ ሰማያዊ ሕይወትን ተስፋ አደርጋለሁ ማለት እንደሆነ የኢትዮጵያ ሊቃውንት ያትታሉ ። ስለዚህም ቤተ ክርስቲያናችን ይህን ምልክት በአንገቱ ላይ በማድረግ አባልነቱን ታጸናለታለች ።

## ከሕዝቡ ልማድ ጋር ያለው ግንኙነት

የማተብ ማሠር ሁኔታ ከሊቃውንቱ ይልቅ በሕዝቡ ዘንድ በጣም የጠበቀ ሆኖ ይታያል ። ከዚሁም የተነሣ በሕዝባዊ አነጋገር ፅገሌ ማተብ የለውም ሲባል ሃይማኖት የለውም በእምነቱ ያልጠበቀ ወላዋይ በተናገረው የማይቆም እግዚአብሔርን የማይፈራ ማለት ሲሆን ፅገሌ ማተብ ያለው ሰው ነው ሲባል ደግሞ ከማለ የማይከዳ የማይዋሽ የማይቀጥፍ እውነቱን እውነት ሐሰቱን ሐሰት የሚል የተናገሩት ከሚጠፉ የወለዱት ይጥፉ በሚለው ምሳሌያዊ አነጋገር ተደግፎ የሚራመድ ማለት ነው ። አሁንም በጊዜያችን በዚህ ሃሣብ የተመሠረተ ባሕላዊ ሙዚቃ/ ዘፈን/ « ባለማተቢቱ« በሚል መነሻ ይጀምራል ፤ የድርሰቱም ጠቅላላ ሃሣብ ወደተቀደሰው ጋብቻ ስትገቢ የሁለታችንንም አንድነት ተረድተሺ ቀይ ስታይ ቀይ ፤ ጥቁር ስታይ ጥቁር ሳትሆኚ በሰላም ልጆችሽን የምታሳድጊው ኢትዮጵያዊት የተባረክሽ ነሽ በማለት በሃይማኖት ክልል ውስጥ ሁና ሲመቻት ብቻ ሳይሆን በመከራም ባለቤቷን አክብራ የምትኖረውን ሴት የሚ

ያሞግስ ነው ። ይህም ራሱ ባለማተብ ማለት በሕዝብ ዘንድ ምንም ያህል ግልጽ እንደሆነ ያስረዳል ።

## ጥቅሙና ጉዳቱ

ማተብ ማሠር በኢትዮጵያውያን ክርስቲያኖች ዘንድ ለብዙ ጊዜ ጸንቶ ለመኖር የቻለው ጥቅሙ የጐላ ሆኖ በመገኘቱ ነው ። ለአንድ ሀገር አንድ ሰንደቅ ዓላማ ለአንድ መሥሪያ ቤትም አንድ ዓይነት የጽሑፍ ምልክት ወይም አርማ እንደሚያስፈልገው ሁሉ በአንድ ሃይማኖት ጥላ ሥር ላለ ሕዝብም አንድ ዓይነት ምልክት በማስፈለጉ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አባሎችም በዚሁ ምልክት ሲጠቀሙ ቆይተዋል ፤ አሁንም በመጠቀም ላይ ይገኛሉ ። ይህ ምልክት በሀገራችን በሃይማኖት አንድነት የሌላቸው ሁሉ በአንድነት ሊፈጽሙት የማይገባቸውን ከመፈጸም እንዲድኑ ከማድረጉ በላይ አንድ መንገደኛ ሰው ሞቶ በተገኘ ጊዜ ክርስቲያንነቱ በዚሁ ምልክት አመልካችነት ተረጋግጦ አስፈላጊው ጸሎተ ፍትሐት ተደርጎለት በዐፀደ ቤተ ክርስቲያን እንዲቀበር በማድረግ ሲያገለግል ቆይቷል ።

በጊዜያችን ግን ሃይማኖት በልብ ነው ምልክትም አያስፈልገውም በማለት በዚህ ምልክት የማይጠቀሙት እየበረከቱ ሄደዋል ። የሚሰጡትም ምክንያት ጽዳት ያጐላል የሚል ነው ፤ ጽዳት የማጉደሉ ሁኔታ ግን እንዳያያዙ ነው ፤ የ ሚፈለገው ምልክትነቱ ነው እንጂ አንዳንዶቹ እንደሚያደርጉት ያሥራ አምስት ክታብ ወይም ግሥንግሥ መሰብሰቢያ ማድረግ አይደለም ። ቤተ ክርስቲ ናችን ግን በሥነ ሥርዓቷ ብትፈጽመውና አስፈላጊነቱንም ብትገልጽ አንዱን ክርስቲያን ይህን ምልክት ሳታደርግ ቀረህ ብላ ከአባልነት አትለየውም አታወ ግዘውም ።

## ማ ጠ ቃ ለ ያ

ማተብ ማሠር ከዚህ በላይ በተገለጸው መሠረት ጥቅሙ በሊቃውንቱና በሕዝቡ ዘንድ ተጠንቶ ለብዙ ጊዜ ቢሠራበትም የተጀመረው ምናልባት በተሳቱ ቅዱሳን ጊዜ ይሆናል ተብሎ ከመገመቱ በቀር በዚህ ጊዜ ተጀመረ ፅገሌ አጸደቀው አስተማረው የሚል በቂ መረጃ ማግኘት አልተቻለም ። ያንዳንድ ሰዎች አስተያየት ደግሞ ምልክትነቱ ተደጋፊ ሆኖ ሳለ ደህና ቦታ ስለአላገኘ አገልግሎቱ አጭር ነው የሚል ነው ። ይህ አንድ ተደጋፊ አስተያየት ቢሆንም ነገሩን ችላ ለማለት ተተኪውን አስቀድሞ ማዘጋጀት ያስፈልጋል ።

አእምሮ ማንደፍሮ ።